የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

EPPF

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ መግለጫ

ቀን ፦ግንቦት 8/2010

## ግንቦት 7 የወያኔን ጉያ ለማሞቅ ደጅ እየጠና መሆኑ ተረጋገጠ!

'' የሞኝ ለቅሶ መልሶ መላልሶ '' ዛሬን ሲጠየቁ ነገን ጭምር በመካድ የተካኑት የግንቦት 7 ሰራ አስፈቺ በስምህ እየተደራደረ በመሆኑ ባለህበት በንቃትና ትጋት አደራህን ጠብቅ።

የነጻነት ጮራ ፈንጣቂና የፍትህና ዲሞክራሲ ቀንዲሎቻችን ተከዜን እንደተሻገሩ በግንቦት 7 ጠቋሚነት ግንባራቸውን ለጥይት የተሰጡት ጅግኖቻችን የአሞራ ሲሳይ እንደሆኑ ደማቸው ሳይደርቅና ስጋቸው ሳይፈርስ ግንቦት 7 ጦሬን ይዤ እግባለሁ በማለት ከነባር የወያኔ ካድሬዎች ጋር በሚስጢር መደራደር መጀመሩን

ለዚህ ሁሉ የትግል ውድቀትና የፖለቲካ ኪሳራ ዋና ቀንደኛ ተጠያቂው የወያኔ ባለውለታ የሆነው የስልጣን ችቦ ተሸካሚው የግንቦት 7ቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሓኑ ነጋ ሲሆን ለፈጸመው ክህደትና እምነት ማጉደል ተጠያቂ ነው!!

በሕዝባችን ስም የትግሉ ጋሬጣ ሆኖ በሓሰትና ውሸት የትግል ኪራይ በመሰብሰብ የሓሰት ፊሽካ ከማስነፋት ጀምሮ ደስ ባለው ሰዓት ውህደት ፣ትብብር፣ ሃገር አድን ፣ሀገራዊ ንቅናቄ ወዘተ ስያሜዎች ስንጭበረበር እንደነበረ የአደባባይ ሚስጢር ነው።

አሁን በቅርቡ መቀመጫውን በውጭ ያደረገውና ODF / የ ኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር፣ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በተደረገ ድርድር መሰረት ኢትዮጵያ ገብቶ በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ ሲል የኦሮሞ ዲሞክራሲ ግንባር በመግለጫው ኣስታውቋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

በቀድሞው ኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር መሪ ሌንጮ ለታ የሚመራው ODF ከ አመት በፊት ከአርበኞች ግንቦት 7 ጋር አብሮ ለመስራት ተስማምቶ የነበረና፣ በሁዋላም

በኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ ውስጥ አባል ሆኖ በየቦታው ገንዘብ ለማሰባሰብ በየሃገራቱ በስማችን ሲነግድ ፣ሲያስነግድና የጀግኖቻችን ፎቶ ለጨረታ እያቀረበ የሰበሰበውን ገንዘብ ለግል ወጪውና ወርሓዊ ደሞዙ ለማዋሉ ዋቢ አያሻውም።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ለእውነትና ሰላም የምትታገሉ የሃገራችን ዜጎች `` የሕዝባችን ዋጋ የሕዝባችን ነጻነትና የእኛም ሰላማችን ነው !

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር አመራሮችና አባላት ላይ  በግንቦት 7ቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሓኑ ነጋ እና በስራ አስፈቺ አባሮቹ  ትዕዛዝ ከአሉበት የትግል ሜዳ እንዲሰደዱና ወደ ሃገር እንዲገቡ መግደልንና ማሳሰረን ጨምሮ ትጥቃቸውን በማስፈታት ሞባይላቸውን አስገድዶ በመረከብ ጥቂት የማይባሉ አመራሮች በሓሰት በመወንጀል ላይ ይገኛሉ።

በመሆኑም ከዚህ ቀደም እንደገለጽነው ሁሉ ግንቦት 7 የተባለው ከሃዲ ቡደንተኛ ስብስብ በምንም መልኩ ብየትኛውም ቦታ እንደማይወክለን በድጋሜ እያረጋገጥን ከዚህ ቀደም በስማችንና በአባሎቻችን አማካኝነት የተሰበሰበውን ቁሳቁስና ገንዘብ አስመራም ይሁን አሬና ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ አስረክበው ስፍራውን እንዲለቁ አበክረን እናሳስባለን።

አንድነት ሃይል ነው

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር